# ምቹ ተፈጥሮ እያላት ምግብ የሚታደልባት አገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት – ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ በርሄ (የምጣኔ ሃብት ምሁር)

March 7, 2017

- *ቦትስዋና 90 በመቶ መሬቷ በረሃማ ነው፤ ግን ራሳቸውን ይቀልባሉ ደቡብ አፍሪካ በድርቅ ተጠቂ ብትሆንም የተትረፈረፈ ምርት አምራች ናት*

***ለምንድን ነው ድርቅ የሚያስከትለውን አደጋ መከላከል ያቃተን?***

*በመጀመሪያ ደረጃ መታየት ያለበት ሀገሪቱ ምን አይነት አቅም አላት የሚለው ነው፡፡ ኢትዮጵያ 70 ሚሊዮን ሄክታር የሚታረስ መሬት አላት ያለው ራሱ የግብርና ሚኒስቴር ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ቢበዛ 14 በመቶውን ነው እየተጠቀምን ያለነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፤ ወንዞቻችን በየዓመቱ 122 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ውሃ ይዘው ከሀገር ይወጣሉ፡፡ እንደውም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ማማ ነው የምትባለው፡፡ በአራቱም አቅጣጫ ነው ውሃ ወደ ውጭ የምንልከው፡፡ ከዚህ በመነሳት እኛ በድርቅ ስንቸገር ብዙዎች ግራ እየገባቸው "እነዚህ ሰዎች ምን ሆነው ነው" ይላሉ። በእርግጥም አስገራሚ ነው፤ በድርቁ የሚጠቁት ቆላማ አካባቢዎች ናቸው፡፡ አንዱ የሶማሌ ክልል ነው፡፡ የሶማሌ ክልል ግን በአለም ላይ በሰፊው ሊታረሱ ከሚችሉ ረጅም ለም መሬት ተብለው ከሚታወቁት አንዱ ነው፡፡ ለም መሬቱ ብቻ አይደለም፤ ዋቢ ሸበሌን ጨምሮ በርካታ ወንዞች፣ ለጥ ባለው ለም መሬት ላይ ዝም ብለው ይፈሳሉ፡፡ የሰዎቹ አኗኗር ሁኔታ ሲታይ ደግሞ አርብቶ አደሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ሰዎች ከአርብቶ አደርነት ወደ አርሶ አደርነት ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ተግዳሮት የሚሆነው፣ ማንም ሰው የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ባህል … በግድ ለመቀየር መብቱ የለውም፡፡*

*በሌላ በኩል ድርቅ በተፈጠረ ቁጥር ለተረጂነት ይጋለጣሉ፡፡ ባለፈው ዓመት ኤሊኖ ሲከሰት ከ8 መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ አውጥቶ ነው መንግስት እርዳታ ያቀረበው፡፡ ይሄ ገንዘብ ወደ ሌላ ልማት ቢውል ኖሮ ብዙ ስራ ይሰራል፡፡ እርግጥ ነው ከምንም በላይ የሰው ህይወት የማዳን ስራ ይቀድማል፤ ግን በዚህ መንገድ እስከ መቼ ነው የምንቀጥለው የሚለው ነው፤ ዋናው ጥያቄ፡፡*

*እኛ ከተወለድን ጀምሮ ኢትዮጵያ በድርቅ ስትመታና ስትቸገር ነው የምናየው፡፡ በ1977 ያ ሁሉ ድርቅ በተከሰተበት ጊዜ፣ 8 ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ ነበር በረሀብ የተጠቃው፡፡ ያኔ እርዳታ በማስተባበሩ ረገድ ትልቁ ተዋናይ ቀይ መስቀል ነበር፡፡ የዓለም ህዝብ ከ1 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጣ እርዳታ ነበር የላከው፡፡ ዛሬም እንዲሁ እርዳታ እየጠየቅን ነው፡፡ ስለዚህ መሰረታዊ መፍትሄ መፈለግ አለበት ማለት ነው፡፡ አንዳንዴ ስለ እንደዚህ አይነት ችግሮች ስንነጋገር፣ የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት አቅማችን ምን ይመስላል … የሚለውንም በመገምገም መሆን አለበት፡፡*

*አንደኛ፤ የሚፈጠሩ አደጋዎች ተተንባይ እንደመሆናቸው፣ ምን ያህል የእርዳታ ክምችት አለን የሚለው ወሳኝ ነው፡፡ የአደጋ ማስተባበር የምንለው ከዚህ በኋላ የሚከተልና የተከማቸውን እህልና እርዳታ፣ ጤንነቱን ጠብቆ ወደየአካባቢው የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ሰዎች ከቀዬአቸው እንዳይሰደዱ፣ በየቦታው የእርዳታ ማቅረቢያ ካምፖች ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መንገድ እርዳታውን በተገቢው ማድረስ ይቻላል፡፡*

*አደጋን ማስወገድ ስንል ደግሞ ከእነአካቴው መሰል ችግር እንዳይከሰት የሚሰራ ስራ ነው፡፡ እኛ ገና እዚህ ላይ አልደረስንም ማለት ነው፤ አሁን ከሚታየው ሁኔታ አንፃር፡፡ ለችግር የተዳረጉ ሰዎች በቀጣይ እንዳይደገምባቸው በደህና ጊዜ ሀብትና ጥሪት የሚያፈሩበት ሁኔታ መፍጠር፣ ከገበያ ገዝተው ራሳቸውን ማስተዳደር የሚችሉበትን አቅም መፍጠር ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ እስካሁን የታሰቡ አይመስልም፡፡ ድርቅ የሚያስከትለውን ጉዳት እንዴት መሻገር እንችላለን ለሚለው አንዱ፣ እነዚህን ዘላቂ መፍትሄዎች ማሰብ መቻል ነው። ከዚህ በፊት የነበሩት፣ የፖሊሲ ችግሮች ጭምር ናቸው፡፡ "የእነሱን ህይወት የመቀየር ኃላፊነት የለብንም፤ እንዳሉ ከጠበቅናቸው በቂ ነው" የሚል ፖሊሲ ነበር፡፡ አሁን ግን የዚያ አይነት ፖሊሲ የለም። በአግባቡ መተግበርና መስራት ግን ያስፈልጋል፡፡*

*በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፣ ሰፋፊ ሜካናይዝድ የግል እርሻዎች ተጀምረው ነበር፡፡ በደርግ ዘመን ተዘግቶ የነበረ ሲሆን አሁን ግን በፖሊሲ ደረጃ እያገገመ ያለ ነው፡፡ ለውጭ ዜጎች መሬት እየተሰጠ ስራ እየሰሩ ነው፡፡ እርግጥ ወደ ውጪ ነው ኤክስፖርት እየተደረገ ያለው፤ ቢሆንም በገንዘቡ ሌላ ምግብ መግዛት እንችላለን፡፡*

*አሁንም ቢሆን ያልነካነው ሰፊ መሬት ጥቅም ላይ ሊውል ወደሚችልበት መንገድ መሄድ አለበት። ኢንቨስተሮች መጥተው፣ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ከዘልማድ አርብቶ አደርነት ወጥቶ የተሻለ አርብቶና አርሶ አደር የሚሆንበት መንገድ*

ቢፈጠር የተሻለ ነው፡፡ ውሃና የግጦሽ መሬት እየተከተለ የሚሄድ ሳይሆን አንድ ቦታ ተረጋግቶ፣ ከብቶቹን በጤንነት ተንከባክቦ ቢያረባ የት በደረሰ ነበር፡፡ በአካባቢው በተለይ በበርበራና በሞቃዲሾ በኩል በአመት ወደ ሶስት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ የቁም እንስሳት በኮንትሮባንድ መልክ ከሃገር ይወጣሉ፡፡ ይሄ ሁሉ ሃብት ያለው ህዝብ ነው፣ አሁን ተራበና ተቸገረ እየተባለ ያለው፡፡ ይሄንን በእቅድ ይዞ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይሄን ደግሞ የግል ዘርፉ ነው መስራት ያለበት፡፡ ለምሳሌ የዚምባብዌን ነጭ ገበሬዎች ሙጋቤ ሲያባርራቸው፣ ወደ ሞዛምቢክ ሄደው በዘጠኝ ወር ነው የሞዛምቢክን የምግብ አቅርቦት በ3 እጥፍ የጨመሩት፡፡

ገበሬ ስንል ዝም ብሎ ልምድ የሌለው፣ አያስፈልግም ማለቴ ነው፡፡ ባንክ ስለሚያበድር ብቻ ሁሉም ገበሬ ነኝ ብሎ መሬት ወስዶ፣ የሃገሪቱን አንጡራ ሃብት ማባከን የለበትም፡፡ ጋምቤላ እየተሠራ ያለውን ስራ እናውቃለን፡፡ ከአፈሩና ከውሃው ጋር የሚጠጣሙ፣ ልምድ ያላቸው፣ ግብርና ከዘር ማንዘራቸው እየተላለፈ የመጣ፣ ስራውን የሚያውቁ ትልልቅ አቅም ያላቸው፣ ገብተው ሊሠሩ ይገባል፡፡ በድርቅ ተጠቅተዋል የተባሉት ቆላማ አካባቢዎች በስጋና በወተት ኢንቨስትመንት፣ ሰፊ አቅም አላቸው፡፡ በዚህ ላይ በትኩረት መሰራት አለመቻሉ፣ ዛሬም ከድርቅ አደጋ እንዳናመልጥ አድርጎናል፡፡ እነሱን ለመርዳት የወጣው 8 መቶ ሚሊዮን ዶላር እና ከውጭ የመጣው እርዳታ ለእንደዚህ አይነቱ ልማት ቢውል፣ እነዚህ ሰዎች ኩሩ ሆነው በኖሩ ነበር፡፡ እርዳታ ሲጠይቅ ማንነቱን አዋርዶ ለማኝ ሆኖ ነው። ለእነዚህ ዜጎች ይሄን አማራጭ ብንተገብርላቸው፣ ከዚህ ሰቀቀን በወጡ ነበር፡፡

እንዴት ነው አቅም መፍጠር የምንችለው?

ዘላቂ መፍትሄ ለማስገኘት የግል ዘርፉ ሰፊ ድርሻ ሊኖረው ይገባል፡፡ የግል ባለሀብቱ ደግሞ ካፒታል ያስፈልገዋል፡፡ ካፒታል ደግሞ አሁን ባሉን ባንኮች ተንቀሳቅሶ ሊሰራበት የሚያስችል አይደለም፡፡ በተለይ የውጭ ኢንቨስተሮች እንዲመጡ ከፈለግን፣ በግሎባላይዜሽን አስተሳሰብ ሁሉም እኩል ካፒታል ይፈልጋል፤ ስለዚህ እነዚህን ማስተናገድ የሚችል የባንክ አቅም ያስፈልገናል፡፡ ለምሳሌ ደቡብ አፍሪካ በድርቅ የምትጠቃ ብትሆንም የተትረፈረፈ ምርት አምራች ነች፡፡ ሀገሪውን የሚቀልቡት ጥቂት ሰዎች ናቸው፡፡ የህዝቡን 3 በመቶ አይሆኑም፤ ሙሉ ደቡብ አፍሪካን የሚቀልቡ ገበሬዎች፡፡ ወተት እንኳ ሳይቀር እንደ ወንዝ ነው የሚያፈሱት፡፡ በቧንቧ መስመር ነው የሚያከፋፍሉት፡፡ እነዚህን ልምድ ያላቸው ገበሬዎች ወደ ሀገራችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ እናምጣ ብንል፣ ባንኮቻችን አቅም የላቸውም፡፡ ኢንቨስተሮች ወደዚች ሀገር ሲመጡ አንዱ የሚጠይቁት፤ "ምን ባንክ አለ?" የሚለውን ነው፡፡ ለዚህ ምላሽ የሚመጥን የባንክ አቅም አልፈጠርንም፡፡

**ለምንድን ነው ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች የማይለሙት?**

ዋናው ችግራችን እንግዲህ ከታሪካችን ይነሳል። ሌሎች ሀገሮች እንደ ደቡብ አፍሪካ፣ ዚምባቡዌ፣ ቦትስዋና፣ ዛምቢያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ … ስንመለከት፣ የኛን ያህል መሬትና የውሃ ሀብት የሌላቸው ናቸው። ግን በቅኝ ግዛት ዘመን የዳበረው ባህል ለዛሬው ጠቅሟቸዋል፡፡ በቅኝ ግዛት ዘመን ሰፋፊ እርሻ የነበራቸው ገበሬዎች፣ የልጅ ልጆች ዛሬም ድረስ ግብርናውን ያከናውሉ፡፡ ለምሳሌ የኬንያን የዱር እንስሳት አስተዳደር ስንመለከት፣ ዛሬም በነጮቹ እጅ ነው ያለው፡፡ ኬንያ ወደ 4 ቢሊዮን ዶላር ከዚህ ዘርፍ ታገኛለች፡፡ እነዚህ ሰዎች ይሄን ቀጥ አድርገው ይዘውላታል ማለት ነው፡፡ ግብፅም ብንሄድ ሰፋፊ የጥጥ እርሻዎች አሁንም ድረስ በእንግሊዞች ኩባንያ ስር ነው ያሉት፡፡ የግብፅ የጥጥ ምርት በአለም ገበያ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

በኛ ሀገር ይሄ ባህልና ታሪክ የለም፡፡ በጃንሆይ ዘመነ መንግስት ሰፋፊ እርሻ ተጀምሮ ነበር፡፡ የበቆሎ፣ የቦሎቄ፣ የሰሊጥ፣ የጥጥ እርሻ በግለሰቦች ተጀምሮ፣ ጥሩ አቅጣጫ ይዞ እያለ ደርግ መጣና ወረሳቸው፡፡ ደርግም የመንግስት የእርሻ ልማት ብሎ ለመቀጠል ሞከረ፡፡ የደርግን ሰፊ ወታደር ሲቀልቡ የነበሩት እነዚህ የመንግስት እርሻዎች ናቸው፡፡ 17 ዓመት ሙሉ ደርግ ለቀለብ ምንም የውጭ እርዳታ አላገኘም፡፡ በ1977 ነው ለህዝቡ እርዳታ የመጣው እንጂ አብዛኛው ቀለብ የሚሰፈረው ከእነዚህ እርሻዎች ነበር፡፡

አሁን ደግሞ በፖሊሲ ደረጃ አነስተኛ አምራቾች ላይ ነው ማተኮር ያለብን ተብሎ፣ የድህነት ቅነሳ መርሃ ግብሩ እስከወጣበት እ.ኤ.አ 2006 ድረስ ሰፋፊ እርሻ የሚባል ነገር ክልክል ነበር፡፡ የነበሩትን የደርግ እርሻዎች ወደ ግል ከማዞር በዘለለ፣ አዳዲስ እርሻዎች አልተጀመሩም ነበር፡፡ ቆይቶ ነው 4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት አለና፣ ኢንቨስተር እንፈልጋለን የተባለው፡፡ ኢንቨስተር ተፈልጎ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ አሁን በቅርቡ እንዳየነው፣ ለእርሻው ብለው ገንዘብ ወስደው ለሌላ ነገር አዋሉ ተብለው፣ ግማሹ ታሰረ ሲባል በየሚዲያው እየሰማን ነበር፡፡ የልማት ባንክም ለእርሻ የሚሰጠውን ብድር ሙሉ ለሙሉ አቁሞ ነበር፡፡ እንደኔ ዋናው የማናጅመንት ጉዳይ ነው፡፡ አሰራሩ ነው መፈተሽ ያለበት፡፡ ለምሳሌ አንድ የህንድ ኩባንያ 3 መቶ ሺህ ሄክታር ወሰደ ተባለ፡፡ ከዚያ መቶ ሺህ ተባለ፡፡ ቀጥሎ ከመቶ ሺው 2 ሺህ ሄክታሩን ብቻ ነው ያለማው ተባለና እንደዚህ አይነት ውጥንቅጥ፣ በአስተዳደሩ ውስጥ ችግር እንዳለ የሚያመለክት ነው፡፡

አንድ ኦክላንድ ኢንስቲትዩት የሚባል አለ። በየቀኑ ነው መንግስት ለውጭ ባለሀብቶች መሬት ሰጠ እያለ የሚወቅሰው፤ ግን ከ4 ሚሊዮን ሄክታሩ የተሰጠው 5መቶ ሺም አይሞላም፤ እሱም ምርታማ አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ ሀገሪቱ ላይ ችግር

ሲፈጠር መፍትሄ ለማምጣት ጥረት አይደረግም። ልማታዊ መንግስት ስንል፣ አንዱ ራሱ መንግስት ነው፡፡ መንግስት – ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሀብት ያቀርባል። ሌላው የግል ዘርፍ ነው – ገንዘብ፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ ይዞ ይመጣል፡፡ ሶስተኛው ባለድርሻ ምሁሩ ነው፡፡ የተሻሉ የምርምር ውጤቶችን ያቀርባል፡፡ እነዚህን ነገሮ ስንመለከት፣ ይሄ እኛ ሀገር አለ ወይ? የሚለውን እንድንጠይቅ እንገደዳለን። በነገራችን ላይ ይሄ ትልቅ ምርምር የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ደቡብ አፍሪካ ሄዶ ልምድ መቅሰም አሊያም ከዚያ ኢንቨስተሮችን መጋበዝ ነው የሚያስፈልገው፡፡ በግብርና ከተሳካላቸው አንዷ ቦትስዋና ነች፡፡ ቦትስዋና 90 በመቶ መሬቷ በረሃማ ነው፣ ግን ራሳቸውን ይቀልባሉ፡፡ አሁን ምቹ ተፈጥሮ እያላት ምግብ የሚታደልባት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት፡፡

እንደኔ፣ ልክ የሀገር ዳር ድንበር ተደፈረ ብለን እንደምንነሳው፣ ይሄም ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ለእነዚህ ነገሮች ቅድሚያ ተሰጥቶ መሰራት አለበት፡፡ ከዚህ ችግር እስከ መጨረሻው መውጣት አለብን፡፡ መንግስት የየአካባቢውን ህዝብ ማስተማር አለበት፡፡ ጉድጓድ ሄዶ መቆፈርና እህል ማቅረብ፣ መቼውንም ቢሆን ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፡፡ መንግስት ራሱ ልምድ ካላቸው ሀገሮች፣ ኢንቨስተሮችን ማምጣት አለበት፡፡ ሲመጡም ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ በሶማሌ ክልል የነበረው የሰላም መደፍረስ ብዙ ችግር ፈጥሮ ነበር፡፡ ያ ገፅታ አሁንም አልደበዘዘም፤ ለዚህ ዋስትና መስጠት ያስፈልጋል፡፡

***መንግስት በሰፋፊ እርሻዎች ኢንቨስት ቢያደርግ … መፍትሄ ያመጣል?***

*የመንግሥት እርሻ ማቋቋም መንግስት ራሱ እንደሚናገረው፣ ካለው የሙስና መንሰራፋትና የመሳሰሉት ጋር ተያይዞ የሚቻል አይመስልም፡፡ ስለዚህ ልምድና ስኬት ያስመዘገበ የግል ባለሀብት ገብቶ እንዲሰራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ቦትስዋና፣ ዚምባብዌ፣ ደቡብ አፍሪካ ወዘተ ከመሳሰሉ ሀገራት የግል ባለሀብቶችን ማምጣት ሁሉ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰፊ ልምድ አላቸው፡፡ አርሶ አደሮቻችንም ወደዚህ ልምድ እንዲገቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በጃንሆይ ዘመን "ጭላሎ አግሪካልቸራል ዲቨሎፕመንት ዩኒቲ" የሚባል ነበረ፡፡ አርሲና ባሌን የስንዴና የገብስ ሀገር ያደረገ ስራ ነው፡፡ የስዊድን መንግስት 4 መቶ ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አድርጎ ያሳደገው እርሻ ነበር፡፡ ይሄ ስኬት ሲያስመዘግብ ደግሞ ወላይታ ላይ እንድገመው ተብሎ፤ "ወላቡ አግሪካልቸራል ዴቨሎፕመንት ዩኒቲ" ተብሎ ተጀመረ፡፡ ያንን ተሞክሮ እንኳ መልሰን ማምጣት አልቻልንም። ደርግ እንዳወደመው ነው አሁንም ያለው፡፡ ይሄ ልምድ መምጣት አለበት፡፡ መንግስት እንዲህ ዓይነት ስኬታማ አሰራሮች እንዲፈጠሩ በቁርጠኝነት መስራት አለበት፡፡ በኢትዮጵያ እርሻውም እየተስፋፋ፣ ኢኮኖሚውም እያደገ ነው፤ ግን ከህዝብ ቁጥር ጋር አልተስማማም፡፡ ለዚህ የሚሆን አቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ የመንግስት ድርሻ ሀገር መጠበቅ፣ ሰላምና መረጋጋት መፍጠር ነው እንጂ ግብርና ውስጥ ይግባ የሚለው አያስኬድም፡፡ ለግል ባለሀብቱ እድሉ ሊመቻች ይገባል፡፡ በከብት ሀብት ከአፍሪካ 1ኛ ነን፤ ግን የደቡብ አፍሪካን ያህል እንኳ አልተጠቀምንበትም፡፡ ምርጥ የከብት ዝርያዎችን ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ዘመናዊ እርባታዎችን መፍጠር አለብን፡፡ የከብት ሀብት አስተዳደራችን መፈተሽ አለበት፡፡ የከብት ሀብት ቢኖረንም ምርታማ አይደሉም፡፡ ይሄም መታየት አለበት፡፡*

**Ethiopatriots**

www.ethiopatriots.com
Mars 7, 2017